ልዩ ትችት ኢትዮሚዲያ

(ትርጉም መላኩ ፀጋዬ መኮንን)

# የተሰበረ የሕጻን አልጋ ዘርጣጭ ብርቱ እጅ!

## የብላቴናው አልጋ ወደቀ

አስመሳይ እሹሩሩ ባይ ሕጻንን
ማማ ላይ ወጥቶ ያሸለበን
ቆጥ አወዛዋዥ ነቅናቂ አልጋውን
ወጀቡ ሲታከል ቅርጫፉ ሲዘም
ይስብራል ቆጡ ይወድቃል ሕጻኑም

እርግጥ ምንም ጥርጣሬ የለም የዛፉ ቅርጣፍ ሲገነደስ የዛፍ ሕይወት ማክተሚያው ይቃረባል። በኢትዮጵያም ሞግዚትና በልጆች አጠባበቅ አያያዝ ላይ ያለው አሰራር የሕፃናት አልጋ የመውደቅ ያህል ይሆናል። በቅርቡ በፈረንሳይ ዜጎች በሁለት ኢትዮጵያዉያን ሕጻነት ላይ የተፈጸመው ዘግናኝና አሳዛኝ የወንጀል ታሪክ ፖሊስ ይፋ አደረገው። አንዱ ገና ሁለት አመቱ ሌላኛዉ ደግሞ የአራት አመት እንቡጥ ሕጻናት ናቸው። በፈረንሳይ ፓሊሲ መግለጫ መሰረት የአራት አመቱ ልጅ “ወድቋል” ተብሎ ወደ ሆስፒታል ለሕክምና መወሰዱና ሀኪሞቹ በፍጥነት ባደረጉት ምርመራ ጉዳቱ ከግብረ-ሰዶሞ ግንኙነት ጋር የተያያዘ መሆኑን አረጋገጡ። ተከታይ ምርመራ የተደረገለት ሌላኛው የሁለት አመት ሕፃንም በተመሳሳይ ሁኔታ በመደፈሩ የተነሳ በሰቃይ ላይ መሆኑ ተረጋገጠ። በዚሁ የተነሳ ጉዳት የደረሰባቸው ሁለቱም ልጆች ለሆስፒታል ተዳርገዋል። የሁሉቱም ሞግዚቶች እስር ቤት ገብተዋል። አባት ሕፃናቱን በግብረሰዶም ግንኙነት በመፈጸሙና በረባሽነት ፀባይ እናት ደግሞ ወንጀሉን ለሕግ ባለማሳወቅ ተከሰው ዘብጥያ ወርደዋል።

ቀዳማዊ ምርመራ ዉጤት እንዳሳዩዉ ሞግዚቶቹ ሕፃናቱን ደቡባዊ ማአከል በሚገኝ ሀቲሎድሬ ከተማ ውስጥ በሲንግዮክስ ክፈል ከተማ ከጥቂት ሳምንታታ በፊት መወሰዳቸው ታውቋል። ሞግዚትነቱ ከኢትዮጵያ ሲውጡ በወያኔ ባለስልጣናት ፀድቆና እውቅና ተሰጥቶት መውጣታቸውም ታውቋል። የልጆቱ አሳዳጊ ሆኖ የወሰዳቸው አባት ተባዬ በአካበቢው ፓሊስ የረባሽነት ባህሪ የተጠናወተው መሆኑን የፓሊስ መዝገብ አረጋግጧል።ታዲያ ይህ ፀባይ ያለበት መሆኑ እየታወቀ በምን ምክንያት በዝምታ ታለፎ ልጆቹ ተሰጡ? እንደዚሁም እንድ አካባቢው ጋዜጣ ሊጆርናል ዲሳዋን ኢትሎሪ ዘገባ መሰረት ሞግዚቶቹ በቂ የሆነ መሰረታዊ እዉቀት እንደሌላቸው ያብራራል።

የአዲስ አበባ የሞግዚት ስርአት ተከታታይ ባለስልጣናት የህንን ጉዳይ ሲስሙ ምንም አልመሰላቸውም፣ ስሜትም አልሰጣቸውም። በሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ስር የሚሰሩት ማህደረ ቢተው ለአሜሪካው የአማርኛ ራዲዩ ጣቢያ ጋዜጠኛ ለትዝታ በላቸዉ እንደገለፁት ስለጉዳዩ የኢትዮጵያን ኤምባሲ በፓረስ ለወደፊቱ ምን መደረግ አለበት ለሚለው መልስ ለማግኘት በመጠባበቅ ላይ እንደነበሩ ገልፀው፣የውጭ ሀገር ሞግዚት ጉዳይ እስከሆነ ድረስ አነዚህን የመሳሰሉ ልጆች የውጭ አሳዳጊ ማግኘት አሰፈላጊ ነው ይህ ካልሆነ ስብሳቢ አጥተው የትም ወድቀው ይቀራሉ፣ይሞታሉ ወይም ያለ አይዞህ ባይ በየጎዳናዉ በረንዳ አዳሪ ይሆናሉ ።

አቶ ተስፋዬ ከበደ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ሀገር መግዚቶች ተወካይ በበኩላቸው የሞግዚትነቱ ስርአት ትክክል መሆኑን በማንሳት ተከላክለዋል። በዚሁም ገለፃቸው ልጆቹን የወሰዱት ሞግዚት ወላጆች በፈረንሳይ መንግስት ባለስጣናት ግለሰቦቹ ልጆቹን ለማሳደግ የአእምሮና የአካልም ብቃት ያላቸው መሆኑን አረጋግጠዋል ይላሉ። በልጆቹ ላይ ስለደረሰው አጋጣሚ ግን ሀዘናቸዉን አልሸሸጉም። ነገር ግን በማታለል ማስወጣትን በተመለከተ ምንም ሃላፊነት እንደሌለባቸውና የእሳቸዉ የስራ ድርሻ ወደ ፈረንሳይ ሀገር በሞግዚት የሚወስዱ ልጆችን የወረቀት ስራና መረጃ በትክክል መያዙን ማረጋግጥ ነው ብለዋል። ማህደር ቢተውና ተስፋየ ከበደ ሁለቱም ያሰመሩበት ጉዳይ ለፍቶት ብለው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በልጆች ላይ ይህንን ተግባር የሚፈፅሙ እጅግ በጣም አነስተኛ

*ቁጥር ያላቸው መሆኑ ላይ ነው ይላሉ። ይህንን ቃለ-መጠይቅ የተከታተሉ የተለያዩ አድማጮች አስተያየት መሰረት የባለስልጣናቱ አነጋገር በመጨረሻዋ የአለም ደሀ ሀገር ሕፃናት ላይ ስለተፈጸመ አስከፊ ጥቃት የሚናገሩ ሳይሆን የችካነ የንግድ ምክር ቤት ባለስልጣናት የሸቀጣ ሸቀጥ ገበያን ልውውጥ ላይ የሚሰነዝሩትን አነጋገር የመሰለ ነው የሚጥቀሙት ይላሉ።*

## *በኢትዮጵያ ተንከባካቢ ያጡ ልጆች ችግር-- ወይም የሴናተር ኢንሆፍ የተዛባ አመለካከት አባዜ*

*የኢትዮጵያ ልጆች በተለይ ሴቶችን በተመለከት እንደ ኦክላሆማ ሴነተር ጀምስ ኢንሆፍ ያሉባቸውን ችግር የገለፀ የለም።ጀምስ ኢንሆፍ በአሜሪካ ምክር ቤት በከፍተኛ ደረጃ ለህዝብ በተሰራጨ ንግግራቸዉ፣ ልጃቸው ከኢትዮጵያ አንዲት ሕፃን ልጅን እንዴት አድርጋ ሞግዚት ልትሆናትእንደቻለችና በአሳዳጊ እናትነት እንዳመጣቻት ሲናገሩ፣ ሕጻኗ ከውሻ ከመበላት አድና የታደገቻት መሆኑን እንዲህ በማለት ነዉ የገለጹት፣*

> *“በአፍሪካ ሴት ልጆችን መወርወር አዲስ ነገር አይደለም። ከሶስት ቀናት በኃላ ሲሞቱ ሬሳቸዉን ውሻ ይበላቸዋል።ከዛሬ ስድስት አመት በፊት በአዲስ አበባ አንድ ሕፃን አገኘን። እርሷም የሶስት ቀን ጨቅላ ነበረች። ሕፃኗ ጎዳና ላይ ተጥላ በሞት አፋፍ ላይ እንዳለችና ዉሻ ሳያገኛት እኛ ቀድመን አገኘናት። ይች ህፃን አሁን ልጆ ሞግዚት ሆናታለች። እኔም 20 ልጆችና የልጅ ልጆች አሉኝ። ይህም እጅግ በጣም የምኮራበት ነው። ልጆ ሞሊ ወንድ ልጆች ብቻ ነው ያሏት። ሴት አልነበራትም። ሁል ጊዜ ሴት ልጅ እንዲኖራት ትመኝ ነበር። በመሆኑም ይችን ሕፃን በቅርብ ጊዜ ከኢትዮጵያ አመጣናት አሁን በጥሩ ጤንነትና እንክብካቤ እያሳደግናት ነው። ጤነኛ ነች። አሁን እኔም የሞግዚት የልጅ ልጆ አያት ሆኛለሁ”*

*ሴናተር ኢንሆፍ ከተምታታና ከእዉነት የራቀ የስም ልጠፋቸው በመለስ ዛሬ በኢትዮጵያ ሕፃናት ደህንነት ላይ መሰረታዊ የሆነ ችግር መኖሩን የተረዱ ይመሰላል። ኢንሆፍ የሚሉት ለአእምሮ ዘግናኝ ነገር እውነት ከሆነ የመለስ አገዛዝ ሕፃናትን ውሻ እንዲቆረጥማቸዉ በማድርግ ወንጅል ሊከሰስ ይገባል። የኢንሆፍን ምስክርነት ውሰዱ፣ እዉን ዛሬ ሀገር እያቋረጡ የሚመጡ የሕፃናት ሞግዚቶች ልጆቹን ቢደፍሯቸው ያስገርማልን? ጉዳዩ አብዛኛው የድህ ልጅች በትልቅ አደጋ ላይ ወድቀዋል። በዚህም ረገድ ኢትዮጵያ በፍጥነት “በአለም ደረጃ የከፋ የሕፃናት ጠላት ሀገር” ወደመሆን ተለወጣለች።*

*የአገዛዙ በሕፃናት አስተዳደግ ላይ በጣም የኮሰመነ ትኩረት ነው ያለው። የዚህም ውጤት የውጭ ሞግዚት አሳዳጊዎችን በተመለከተ መመሪያ የለውም። በመሆኑም አስዳጊ ያጡ፤ የተገለሉ፤ የታረዙና የተገፋ ልጆች “በሕፃናት ደላላዎች” በደል እየተፈጸመባቸው ነው። አሁን የሚታየው አህዝና ትንታኔ በቅርብ አመታት የውጭ ሀገራት የኢትዮጵያ ሕፃናት በአሳዳጊነት መውሰድ በፈጥነት እያደገ የመጣ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ በአውሮፓ የሞግዚት ድርጅቶች ስር ከሚገኙ ሕፃናት ከቻይና ቀጥላ ሁለተኛ ደረጃ ስትይዝ በአሜሪካ ደግሞ ልጆች ሞግዚት እያገኙ በመሄድ አራተኛ ደረጃ ይዛለች።*

*አንድ ጊዜ ወደ ውጭ ሀገር ለሞግዚት አሳልፍው ከተሰጡ በኃላ የልጆቹን ሁኔታ የመከታታል ነገር ከቶ የለም። ተጨባጭ ታሪኮች እንደሚያመለክቱት ለሞግዚት የተሰጡት ልጆች መካከል ብዙዎች ያልተመቻቸው መኖራቸው ግልጽ ነው። ለምሳሌ በአሜሪካ የሚቀርቡ ዘገባዎች ሞግዚት ሆነው ያመጡአቸው አሳዳጊዎች የሚያባርሯቸው ልጆች በርካታ ናቸው። ልጆቹም በሚደርስባቸው መገለልና መሰቃየት የተነሳ በርካታ የባህሪ ለውጥ ያመጣሉ፤ በመጨረሻም የታደጊዎች ፀባይ ማረሚያ ቤት የሚገቡ ብዙ ናቸው። በሞግዚት ስር የወደቁት ልጆች ከሞግዚታቸው ባሻገር ከሌላው የሰው ፍጡር ጋር የሻከረ ግንኙነት የሚፈጥር ባህር ያሳድጋሉ። ሌሎችም ተከታታይ ጉዳት ሲደርስባቸው ስር የሰደደ የማህበራዊ ጥላቻ ያድርባቸዋል። የአሳዳጊ አሰጣጥ ችግር ሌላም ጉድለት አለበት። ይኸውም በድብቅ የሚከናወን የሕፃናት ሕገወጥ አስጣጥ እንደ አለማቀፍ የስደተኞች ድርጅት የኢትዮጵያ አስተባባሪ አቶ ይጥናው ጌታቸው አባባል የሕገወጥ የሕፃናት ሽግግር በ10ሽህዎች የሚቆጠሩትን እንዳጋዘ ይናገራሉ። በቅርብ ጊዜ ለአሜሪካ ሬዲዮ ጣቢያ በሰጡት መግለጫ አሽጋጋሪ ደላላዎች በደሀው የገጠር ቤተሰቦች ድረስ በመሄድ የልጆች ጓደኛ በመምሰል ወደ ጠቅላይ ግዛት ከተሞች ሂደው ትምህርትና የሥራ እድል*

እንደሚያስጡአቸውና የተሻለ ኑሮ እንደሚያገኙ በመግለፅ አታለው ከአካባቢያቸው እንደሚያስኮበልሉ ተናግረዋል።

የልጆች ኮንትሮባንድ በኢትዮጵያ ውስጥ በጣም አትራፊ ንግድ ሆኖ መገኘቱና በልጅ እስከ $800 የአሜሪካ ዶላር ወይም ስምንት ሺህ ብር በላይ ያገኙበታል። እንደ አንድ ጥናት ጥቆማ በየአመቱ በሺህዎች የሚቆጠሩ ልጃገረዶችና ሴቶች ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሀገሮች ማለትም ሊባኖስ፤ ሳውዲ አረቢያ እና የተባበሩት የአረብ ኤምሬት የመሳሰሉ ሀገራት የቤት ሰራተኛ  ትሆናላችሁ ተብለው የተወሰዱ ብዙዎች ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ልጆች በመጨረሻ ሴተኛ አዳሪ እንዲሆኑ የተገደዱና በርካታ ቁጥር ያላቸው ደግሞ በቤት ሠራተኛነት የተቀጠሩም ቢሆን በአሰሪዎቻቸው በግዳጅ የወሲብ ግንኙነት ይፈጽሙባቸዋል፤ አካላዊ ጉዳትም ያደርሱባቸዋል፤ አንዳዶች ከሚደርስባቸው በደል የተነሳ እራሳቸውን ያጠፋሉ። በቅርቡ በተሰራጨ መረጃ መሠረት ይህን አይነት ሕገወጥ የሰወች የሽግግር ሥራ የሚያከናውኑ በተደራጀ መልኩ ሕገውጥ የልደት መረጃ የሚስጡ፤ መታወቂያ የሚያዘጋጁና ሌሎች ተመሳሳይ የፈጠራ መረጃዎችን የሚሰሩ መኖራቸው ተነግሯል።

አንዱ የሰዎች ወደ ሌላ ሀገር ያልስርአት መሄድ ችግሩ የጎዳና ተዳዳሪ ልጆች ጉዳይ ሲሆን በመቶሺዎች የሚቆጠሩ በመላ ሀገሪቱ እንደሚገኙ ይገመታል። በአ.አ. ከተማ ብቻ እንደ አንድ ድርጅት ጥናት መረጃ ከ50ሺህ - 60 ሽህ የሚገመቱ የጎዳና አዳሪ ልጆች እንድሚገኙ ይገልፃል። እነዚህ ልጆች ለግዳጅ ሥራና ለፍቶት በከፍተኛ ድረጃ የተጋለጡ ናቸው።

## የሕፃናት ሞግዚት አሰጣጥና ሕገወጥ የስዎች ሽግግርን ለማስተካከል ብቁ ያልሆነ አገዛዝ

የማይታበለው እውነታ አገዛዙ ካሰበበት የሕፃናትን ሕገወጥ ሞግዚትነት ( ሽግግር) ለማስቆም የሚያስችል በቂ የሆነ የሕግ ስርዓት መኖሩ የታወቀ ነው። ለምሳሌ ሕገ-መንግሥቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሰውን ልጅ በማንኛውም መልኩ በሕገወጥ መንገድ ማሽጋገር የትከለከለ ነው ይላል። የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የሚለው ደግሞ “ሴቶችን፤ ሕፃናትንና ወጣት ሰዎችን” ያለ ሕግ ፈቃድ መውሰድ ከ5-10 አመት ያስቀጣል ሲል ደንግጓል። በማታለል፤ በማጭበርበርና ቃል በመግባት በመሳሰሉት ሁኔታዎች ግለሰቦቹ ፈቃደኛ ቢሆኑም እንኳ ማቃጠር፤ ማባበል፤ መንገድ ማሳየትና ማመቻቸት፤ ቤትን መስጠትና መፍቀድ የሕግ ጥሰት ሲሆን ቅጣትም ያስከትላል። “የሞራል ስብዕናን በመዳፈር ማመቻቸት” የሞራል ውድቀት እንዲከተል የማድረግ ወንጅል መፈፅም በውጭ ሀገርም ሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሀገር መባረር ወይም ከአካባቢ መፈናቀልን ያስከትላል። አገዛዙ በሕገወጥ ዘዴ የልጆችን ከሀገር መውጣት መቆጣጠር ከፈለገ እና ትክክለኛ የሀገር መውጫ ስልት ልከተል ካለ የሕግ ስርዓቱ  በቀላሉ በተግባር እንዲተረጎም ማስቻል ነው።

አገዛዙ ግን ችግሩን በትክክል ከመፍታት ይልቅ የይታ ስራን ይምርጣል። አንድ መረጃ እንደገለጸው፤ አገዛዙ በቅርብ ጊዜ ያቋቋመው የልጆችን ሕገውጥ ሞግዚት የሚከታተል፤ መረጃ የሚሰባስብ፤ ሕፃናትን የሚያስኮበልሉ፤ የሚነጥቁ ሰዎችን እየተከታተለ የሚያስር ግብረሃይል ማቋቋሙ ተጠቁሟል። አንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከዚሁ ግብረሃይል ጋር በመተባበር የሕገወጥ ፍንገላ ተጎጅ የሆኑ ልጆችን ከቤተሰቦቻቸው ጋር ለማገናኘት ከግብረሃይሉ ጋር አብረው ለመሥራት እንደተቀላቀሉ ተጠቅሷል። ሻምበል አፀደ ወርዶፋ የአ.አ. ፖሊስ ባልደረባና የግብረሃይሉ አባል ከፍተኛውን የሕፃናት ሕገወጥ ሽግግርን ለማስቆምና አጥፊዎችን ለሕግ ለማቅረብ የሰው ሃይልና የገንዘብ እጥረት እንዳለባቸው ገልፀው በተለይ በአሁኑ ይዞታ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ችግር ለመቅረፍ በትልቅ ጋቢ ላይ እራፊ ጨርቅ እንደመለጠፍ ዓይንት ነው ብለውታል።

## ሕጻኑን ውሃው ሳይደርቅ ከመታጠቢያ ገንዳው አታውጣው

በኢትዮጵያ ሕፃናት ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉባቸው ጉዳዮች በጥልቀት እናውቃለን። የኤድስ እና ኤችአይቪ ስርጭት፤ ድርቅ፤ እርዛት የመሳስሉት ችግሮች በደሃው የገጠር ነዋሪዎች ላይ ከመጠን በላይ ያደረሱትን ጉዳት የማንረዳ አዕምሮ ቢሶችም አይደለንም። በርካታ ልጆችን ያላሳዳጊ አስቀርቷል። ለሕገወጥ ተግባር ልጆች እንዲዳረጉ አጋልጧል።

ምንም ጥርጥር የለንም የውጭ ሞግዚቶች ለልጆቹ የተሻለ እድል ይሰጡአቸዋል። ይህ ካልሆነ የችግር ሕይወት ይገጥማቸዋል።እዚህ ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ሕፃናት ላልተጠበቀ ችግር የዳረጋቸው የአገዛዙ የችግር መፍትሄ አወሳሰድ የተለየ መሆኑ ነው። ብዙ ሀገሮች ተመሳሳይ ችግር እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ ያላቸው ወሳኝ እርምጃ ወስደዋል። ለምሳሌ ቻይና የሞግዚት አስጣጥ ስርዓቷን ሙሉ በሙሉ ቀይራለች። ከብዙዎቹ መካከል ሞግዚት የሚሆኑ ወገኖች በተደጋጋሚ ልጆቹን ወደ ሀገር ለማምጣትና ሀገራቸውን እንዳይረሱ የማድረግ ውል አንዱ ነው። በዩክሬን ደግሞ አሜሪካ በሞግዚትነት የውሰደቻችው ልጆች በኢምባሲ አማካይነት ደህንነታቸውን የሚያረጋግጥና ልዩ ክትትል የሚያደርግ ተከታታይ ድርጅት አቋቁማለች። ቬትናም በበኩሏ በሞግዚት ለመውሰድ የሚፈልግ ሀገር የተወሰኑ የግዴታ ውሎችን ለሚገቡ ብቻ ይሰጣሉ። ከዛኪስታን ሳይቀር ለግለሰቦች የሞግዚት መስጠትን በህግ ከልክላለች እውቅና ያላቸው ድርጅቶች በሞግዚት የውሰዱአቸውን ልጆች ይዞታ ተከታታይ ዘገባ የሚያቀርቡ ብቻ እንዲወስዱ ትፈቅዳለች። በአለማቀፍ ደረጃ የልጆችና የሴቶችን ኮንትሮባንድ የሚከላከለውን የፓላሪሞ ፕሮቶኮል 118 ሀገራት ሲፈርሙ ኢትዮጵያ ግን አልፈረመችም።

## ልጆች ሰብአዊ መብት አላቸው! የሕፃንነት መብት ድንጋጌ

ኢትዮጵያ የልጆችን መብት ድንጋጌ የተቀበለች ሀገር ናት። ነገር ግን መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በሰፊው የሕፃናት መብት የማይጠበቅበት፤ የማይከበርበት ይኸውም ልጆች ከመሰቃየትና ከብዝበዛ ነፃ መሆንን የተመለከተውን ውል ጨምሮ በተግባር ገሸሽ የተደረገበትና የተጣሰበት ሁኔታ ነው ያለው። አገዛዙ መሰረታዊ ግዲታውን በሕፃናት መብት ድንጋጌ መሰረት አልተወጣም ይኸውም በብሄራዊ ደረጃ በተናጠልም ወይም በጋራ የኢትዮጵያ ሕፃናትን ስቆቃ፤ ሕገወጥ ሽያጭ፣ ሽግግር፣የግብረስጋ ግንኙነትን እና የመሳሰሉት ሲፈጸምባቸው መከላከል አልቻለም።

## ኢትዮጵያ የአለማቀፉን የሄግ የሕፃናት ጥበቃን ድንጋጌና ከሀገር ያለህግ ፈቃድ የሚወጡትን የሚመለከተውን የፓላሪሞ ፕሮቶኮልን መፈረም አለባት

አገዛዙ በግድ ከሀገር በልዩ ልዩ ምክንያት የሚወጡትን ልጆች የተለያዩ ችግሮች ለመፍታት እርምጃ መውሰድ አለበት። የሄግ የሕፃናት ጥብቃና ትብብር ድንጋጌ በተለይ ወደ ውጭ በሞግዚት የሚወጡትን ልጆች በተለየ ሁኔታ ለመጠበቅ የተዘጋጀ ድንጋጌ ነው። ኢትዮጵያን ይህን ድንጋጌ መፈረም ከቻለች የሕፃናትን ሽያጭና ሕገወጥ ከሀገር አወጣጥ ለመከላከል ከ75 ሀገራት ጋር በትብብር ትሰራለች። ይኸው ውል ሌላው ጠቀሜታው የምክርር አገልግሎት ለሞግዚት ወላጆች መስጠትን። ሕፃናትን ለመጠበቅ ጠንካራ የሆኑ ድርጅታዊ ግንኙነት መፍጠርን፤ ሞግዚት ከሚሆኑ ድርጅቶች ጋር የሞግዚትን አስጣት እና ከሰጡም በኃላ ክትትልን፤ የመረጃ አሰባሳብን የስልጠና መርህንና ሙያው ብቃትን ያካተቱ ሁኔታወችን ይጨምራል እንደዚሁም ስለልጆቹ የተጠናከረ ዘገባና ከሀገር ስለሚወጡ ልጁችም በቂ ያሰራር ልምድ ማግኘትን ያጠቃልላል።

ድንጋጌው የአስቸኳይ ጣልቃ ገብነትን በተመለከተው አንቀፅ 21(ሐ) ድንጋጌው ሞግዚቱን የሚፈቅደው የላኪ ሀገር መሆኑን ከረጋገጠ በኃላ፤ የልጆቹ ሁኔታ “አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ወደ መጡበት ሀገር እንዲመለሱ የማድረግ ሀላፊነት የላኪው ሀገር መሆኑን የረጋግጣል።” በቅርቡ በፈረንሳይ በሁለቱ በሕጻናቱ ላይ የተፈጸመው የሰዶም ተግባር በተመለከተ የወያኔ አገዛዝ በከፍተኛ ስቃይ ላይ የሚገኙትን ታዳጊ ሕፃናት በፈረንሳይ ሀገር ወደ ሌላ ሞግዚት ቤት ለማዛወር ጥረት ከማድረግ ይልቅ። በአስቸካይ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ማድረግ ይጠበቅበታል።

አገዛዝይ በግድ የተመድን የሕገወጥ ሰዎችን ከሀገር መውጣት የሚከላከል ፕሮቶኮል መፈረም አለበት። በተለይ ሴቶችና ሕፃናት በተመለከተ ከሀገር አልፎ የተደራጀን ወንጀል ለመከላለል (ማለትም የፓላሪሞ ትራፊክ ፕሮቶኮል በተግባር እንዲውል የ1995 ዓ.ም ድንጋጌ) 118 ሀገራት ሲፈርሙብት ድንጋጌውን ኢትዮጵያ ግን አልፈረመችም። ይኸው ስምምነት በሕግ ካገዳቸው ጉዳዮች መካከል ልጆችን ለግብረ ስጋ ግንኙነት መዋልን፤ በሕገወጥ መንገድ ከሀገር የወጡ ልጆች እንዲመለሱ ማድረግ ከዚሁ የልጆች ትራፊክ ጋር በተገናኘ የሚያዙ ንብረቶች እንዲወረሱና የውርሱ ባለቤትም በደል ለደረሰበት ወገን እንዲሰጥ እንዲሁም አግባብነት የሌላቸው

*መረጃዎችን በማቅረብ ተጎጂውን ያላግባብ ሊያጉላሉ ይችላል ተብለው የሚታሰቡ መረጃዎች ሳይቀር እንዲወሰዱ ይኸው ድንጋጌ ያስገድዳል ።*

*በኢትዮጵያ ሕገመንግስት አንቀፅ* 13 *አገዛዙ የኢትዮጵያን ሕፃናት ሰብአዊ መብት የመጠበቅ ግዴታ ሲጥልበትና በአለማቀፍ ድንጋጌ መሠረት ይህንኑ የማስፈጸም ሀላፊንት አለበት። በዚሁ መሠረት አገዛዙ ከሳውዲ አረቢያ፤ ከሊባኖስ፤ ከተባባሩት የአረብ ኤምሬት እና ከሌሎቹ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ጋር የተናጠልና የጋራ ውይይት በማድረግ በሕገወጥ መንገድ ወደነዚህ ሀገራት ስለሚፈልሱት ኢትዮጵያውያን ልጃገረዶች መብት መከራከር አለበት። አገዛዙ የራሱን ሕገመንግስትና የአለማቀፍ ሕግን መሠረት በማድረግ ችግራቸው እንዲፈታ ማድረግ ይገባዋል።*

*በፈረንሳይ ሀገር ሆስፒታል ተኝተው፤ ቋንቋው በማይገባቸው ሰዎች ተከበው የሚገኙትን ሕፃናት ልጆች ሁኔታ ስናስብ ልባችን ይንሰፈሰፋል። እነዚህ ሕጻናት የደረሰባቸውን በደል ለማን እንደሚናገሩ እንኳ አያውቁም። ስቃያቸውን አጠቃላይ መረበሻቸውን የሚያጽናና አይዞህ ባይ ወገን የላቸውም፤ ምንም ጥጥር የለንም የፈረንሳይ የሕክምና ባለሙያዎች በጥሩ ሁኔታ ይንከባከቧቸዋል የሚል እምነት አለን።ሕሊናችን የረበሸው ከዚህ አሳዛኝ ወንጀል በኃላ ፈረንሳይ ለእነዚህ ሁለት ሕጻናት ምጠለያ ሀገር ልትሆናቸው አትችልም። በምንም መልኩ እነዚህ ልጆች ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ በዘላቂነት መመለስ አለባቸው።*

## *የሕፃን አልጋ ፈንጋይ እጅ*

*በኢትዮጵያ ሕፃናት ጉዳይ ላይ ከአገዛዙ ጋር ያለን ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ ሌላው አማራጭ መንግስታዊ ያልሆኑ የለጋሽ ድጋጅቶችን በሕገወጥ መንገድ ከሀገር ስለወጡ ሕፃናት፤ ስለሕገወጥ ሞግዚት ሁኔታ፤ የለጋሽ ድርጅቶች እርዳታ የሚሰጡበትን መንገድ መጠየቅ እንዳይቻል አገዛዙ በአዲስ መልክ የደነገገው የለጋሽ ድርጅቶች መተዳደሪያ ሕግ ድርጅቶቹን እንዳይንቀሳቀሱ አድርጎ አስቀመጣቸው የአሜሪካው ምክር ቤት የአፍሪካ ንዑስ ኮሜቴ ስብሳቢ ሴናተር ሩዝ ሬንጎልድ ለምክር ቤቱ ባደረጉት ንግግር የአገዛዙን አዲስ ሕግ ነቅፈውታል።*

*የኢትዮጵያ መንግስት አዲሱ ሕግ በሀገሪቱ ለሚሠሩ የሲቪል ማህበረሰቦች ለስራቸው ተጠያቂነትንና አሠራራቸውን ጥራት ለማሻሻል ታስቦ የተዘጋጀ ነው ይላል አሁን በነዚህ ድርጅቶች ላይ ጠንከራ ቀጥጥር የሚጣልበት ጊዜና ወቅት አይደለም በተቃራኒው የኢትዮጵያ መንግስት ለጥራታቸውና ለድርጅቶቹ የስራ ብቃት ድጋፍ የሚስጥበት ወቅት ነው። ይኸውም ለሀገሪቱ ፓለቲካዊ፤ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ሂደት መፋጠን መሠረታዊ ጉዳይ ናቸው። በተቃራኒው ግን መንግስት እያደረገ ያለውን ተግባር የተጠያቂነትና የስራ ጥራት ክትትል ለማኮስመን ሆነ ተብሎ የታቀደ ሕግ ነው።*

*“ውሻሉ ሲሳብ አልጋው ላይ ያለውን ልጅ ጨምሮ ሁሉም ነገር ይገለበጣል” አገዛዙ ዛሬ እያደረገ ያለው ሁሉንም ድጋፍ መዘርጠጥና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕፃናትን ደግፎ የያዘው የሕይወት መሠረታቸው እንዲነጥፍ ማድረግ ነው። ያለተገቢ ድጋፍ በማስቀረት የልጆች ሕይወት በየቀኑ እንዲረግፍ የሚያደርግ ሁኔታ እየተፈጠረ ነው።ይህ ግን እኛን አያስደንቀንም። ለምን ቢባል የተሰበረን የሕፃን አልጋ የሚገፈትረው እጅ ሀገሪቱንም እየጣላት ያለው እጅ መሆኑን ስለምናውቅ ነው።*